# ቀስተ ደመና

የሰላምና የወድማማችነት ድምፅ ሬድዮ ጋዜጣ

ቁጥር 1-3 ልዩ እትም መስከረም / ህዳር 1990

## ከአዘጋጅ ብዕር

መስከረም 1 ቀን 1990 ዓ ም ሥርጭቱን የጀመረው የቀስተ ደመና ሬዲዮ፤ የሰላምና የወንድማማችነት ድምፅ የአራት ወራት የአገልግሎት ግዜውን አጠናቅቆ አምስተኛ ውን ወር ሊይዝ ነው።

የቀስተ ደመና ሬዲዮ የሚያስተላልፋቸው ዜናዎች ፤ ትችቶችና ትንተናዎች ፤ ቃለ መጠይቆች ወዘተ በአየር ላይ ውለው ሳይጨበጡ እንደተበተኑ የትም እንዳይቀሩና በፅሁፍ ተቀርፀው ቢቀመጡ ለተደራሲው የሚሰ ጡት ጥቅም የላቀ ይሆናል ብለን በማሰ ብ ፤ ከወራት በፊት አንድ መፅሄት ለመጀመር አቅደን ጊዜ ጊዜን እየወለደ ዛሬ ላይ ደርሰናል።

ባለፉት አራት ወራት ቀስተ ደመና ሬዲዮ ያስተላለፋቸውን ትችቶችና አስተያየቶች በማቀናበር ይህንን 'ልዩ እትም' አዘጋጅተናል። የተለያዩ ለሃገራችን ወቅታዊ ጉዳዮችና ጥያቄዎች ቅድሚያ ትኩረት የሰጡት እነዚህ አስተያየቶች በርካታ ቁም ነገሮች ያስጨብጣሉ የሚል ዕምነት አለን።

የ 'ቀስተ ደመና' ጋዜጣ ከዚህ ልዩ እትም በኋላ በየግዜው እንደሚወጣ ልናበስር እንወዳለን።

መልካም ንባብ !

ቀስተ ደመና ሬዲዮ የሚተላለፍበት ፕሮግራም ገጽ.....................................19

* የኢሃዴግን ጦር ጠማሽ አቋም ላለማገዝ...........
ሰላማዊውን የፖለቲካ ትግል አለማፍዘዝ.......................................4

* የቡድን ውኸ[ር]ንብር ጠቃሚነቱ ለአምባገነኖች ብቻ ነው ................10

* ከፓሪሱ ጉባዔ ያልተቀሰመው ትምህርት..................................3

* ከዶላር ወይስ ከናቅፋ ከጽድቅ ወይስ ከኩነኔ....................9

* ለብቸኛው ልዕለ ኃያል የሚሳነው ነገር አለ ለካ ሄ ሄ.....13

* በነ ዶር ታዬ ላይ በሃሰ ት አልመሰክርም በማለት ራሳቸው በሃሰት የተወነጀሉት ....................15

* ከባሻገሩ ሽግግሩ እንዳያስቸግር..18

* ለነፃ ምርጫ አመች የኃይል ሚዛን መታገል አንገብጋቢ ጥያቄ ነው ................................................6

አስተያየት፤ ትችት፤ ወዘተ ካላችሁ አድራሻችን እንደሚከተለው ነው፤
Radio Rainbow
c/o P.O.Box 140104
53056 Bonn , Germany . Fax : 0049 228 612381

GRAPECA ሰኢአቀ RAGPEHA
Groupe de Recherche et d'Action pour la pain en Ethiopie et dans la Corne de l' Afrique
Research and Action Group for peace in Ethiopia and the Horn of Africa
ሰላም ለኢትዮጵያና አፍሪካ ቀንድ የምርምርና የተግባር ቡድን

# በአደጋላይ ላሉ ዜጎች ትኩረት አልተሰጠም

የህወሃት / ኢህአደግ መንግሥት በተደጋጋሚ ከሚወቀስባቸው ነገሮች ዜጎች አደጋ ላይ ሲወድቁ ትኩረት በመስጠት ግዴታውን አለመወጣቱ ነው። ከዚህ ቮት በ 1987 በተከሰተው ድርቅ ለዜጎች ከቀረበው እርዳታ ይልቅ ለብቸኛ ምርጫው የድምጽ መስጫ ካርዶችና ኮሮጆዎች ሲያድል ተስተውሏል። በ 1988 ደግሞ የአዋሽ ግድብ ከጥንቃቄ ጉድለት የውንጂን ኗሪ በፒርፍ ሲያጥለቀልቅ የተሰጠው እርዳታና ትኩረት እጅግ አሳዛኝ እንደነበረ ሁሉም የሚያስታውሰው ነው።

የኤርትራ ተፈናቃዮች ፤ ከሥራ የተባረሩ የመንግሥት ሠራተኞችን፣ የንግድ ቤት ክራይ አላግባብ ተጨምሮባቸው ጉሮሯቸው የተዘጋ ድሃ ነጋዴዎችና መሬት የተነጠቁ ገበሬዎች አቤቱታና ሮሮ የኢህአደግን ባለስልጣናት ልብ አላራራም።

በቅርቡም ርሃብና ችግር የተሰጠው ትኩረት እጅግ ያነሰ በመሆኑ መንግሥትን አስወቅሷል ። አሁን ደግሞ በጎርፍ በመጎዳት ያለው የሕዝብ ቁጥር በቀላሉ የሚገመት አይደለም። በተለይም የሱማሌ ክልል ሕዝብ ከብቱና ሰብሉ ወድሟል። ራሱም በጎርፍ ተከቦ ትልቅ ችግር ላይ ይገኛል። ሌላውም የአፋር፣ የሰሜንና የደቡብ ሕዝብ ሰብሉ ሜዳ ላይ ቀርቷል። ይህ ከባድ ብሄራዊ አደጋ አስቸኳይ ርምጃንና ብሄራዊ ርብርቦሽን የሚጠይቅ ሆኖ እያለ የህወሃት መንግሥት ሃገሪቱን የከፋ ነገር እንዳልገጠማት ሁሉ ትኩረቱ ሌላ ሆኖ እናገኘዋለን። ለጥቂት የኢህአደግ መሪ ግለሰቦች ምቾትና መቀማጠል ከሚባክነውና ከሚረጨው ሃብት ቀነስ እንኳን እየተደረገ ለችግረኞች ማዋል ያስቸግረው ይመስላል። የሃገር መሪ ነን ባዮች ለእንደዚህ አይነቱ ችግር ቅድሚያ አለመስጠታቸው በህዝብ ላይ የባሰ ችግር የሚያመጣ ወንጀል እንደመሆኑ መጠን ነገ እነሱም እንደግፈኞቹ ሥርዓቶች ከህዝብ ፊት ከተጠያቂነት እንደማያመልጡ ግልፅ ነው////

# ከባሻገሩ ሽግግሩ እንዳያስቸግር

ደሞክራሲያዊ የሆኑ የኢህአደግ ተቃዋሚ ኃይሉች በአንድነት ተባብረው ቢታገሉ የዚህን ፀረ ህዝብ ቡድን እድሜ ለማሳጠር ሲችሉ ይህ የትግል አንድነት ጉዳይ ለኢትዮጵያ ህዝብ የውሃ ሽታ ሆኖበታል። ይህ የተሰበጣጠረ ትግል እድሜውን ለማራዘም እንዳልረዳው ሁሉ "ጠንካራና የሚፈልገውን የሚያውቅ ተቃዋሚ ኃይል አጣሁ " እያሉ ሲያሾፉ መለስ ዜናዊ በተደጋጋሚ ተደምጠዋል። አቶ ዳዊት ዮሐንስም በቅርቡ አሜሪካን ሲጎበኙ ፤ ሰልፍ የወጣውን ተቃዋሚ ምን ያህል እንደሚንቁ ለማሳየት " እንዲህ ስትንጫጩ ይኸው ስድስት አመት ገዛናችሁ " በማለት አሹፈዋል።

የውጭ አገር የኢህአደግ ደጋፊዎችም ለዚህ ጭፍን ወገናዊነታቸው ሰበብ አርገው የያዙት ይህንን የተቃዋሚ ኃይሉችን አማራጭ የማቅረብ አለመቻል እንደሆነ ሁላችንም የምናውቀው ነው። ክርክራቸውን ደጋግመን ሰምተነዋል። "ጭፍን ተቃውሞን ተበታትኖ ከማሰማት ሌላ ምን ታውቃላችሁ? ኢህአደግ ይውደም ከማለት በላይ ምን የምትሉትስ ነገር አለ? የምታቀርቡትስ አማራጭ ምንድን ነው?"

አማራጭ የላቸውም የሚለውን አነጋገር ከሁለት አንፃር መመልከት ይቻላል። አማራጭ ስ ባል ተቃዋሚ ኃይሉች ስለ ነገይቱ ኢትዮጵያ የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚ ፤ የፖለቲካ ፖሊሲዎችና ገጽታዎች ላይ እንደአንድ ሰው ተስማምተው አንድ ፕሮግራም አላወጡም ለማለት ከሆነ ይህ የሚቻል ነገር አይደለም። ሀገራችን እንደማንኛውም ህብረተሰብ በኢኮኖሚ ጥቅም፣ በማህበራዊ ራዕይ፣ በርእዮተዓለም የተለያየ አቅዋሞች የሚያንጸባርቁ ኃይሉችን አቅፋ የያዘች አገር ነች። በነዚህ ላይ የጋራ አቋምና አማራጭ ይዛችሁ ቅረቡ ማለት ሱሪ ባንገት አጥልቁ ማለት ነውና አይቻልም።

የጋራ አማራጭ አቅርቡ ቢባል ካባሻገሩ በኋላ የሚከተሉት ልዩነቶችን ለህዝብ ውሳኔ ትታችሁ ሽግግሩን በተመለከተ የጋራ አቋም ይኑራችሁ ከተባለ ግን ነገሩ ግልጽ ነው። ከ አማራጭም አማራጭ አለ። በተለይ ከፓሪሱ ጉባዔና ከዚያም ተከትሉ በአማራጭ ኃይሉች ምክር ቤት መቋቋም ሳቢያ በሃገሪቱ አሉ የሚባሉ ድርጅቶች ሽግግሩን አስመልክተው ያቀረቡት አማራጭ ሂደት ነጻና ርዕታዊ ምርጫ የሚል ነው። በእጅ ያለ ወርቅ እንደመዳብ ሆኖ ልብ አልተባለም እንጂ እነዚህ ተቃዋሚ ኃይሉች ከሽግግሩም ጥያቄ አልፈው ዘልቀው ሄደው

ስምምነት ላይ ደርሰዋል። በዚህ የሽግግር ምርጫ አማካኝነት በኢትዮጵያ የመድበለ ፓርቲ ስርዓት እንዲኖር፤ ይህ ሥርዓት በሕዝቡ ተቀባይነት ባገኘ ደሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት ላይ እንዲገነባ ለመታገል አጠቃላይ ስምምነት አለ። እንድያውም ይህ መጪው ሕገ መንግሥታችን በርግጥ ደሞክራሲያዊ እንዲሆን የግድ ምን ምን አይነት መብቶችን ማካተት እንደሚኖርበት ስ ባቱም የፓሪስ ድርጅቶችና አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤትም ስምምነት ላይ ደርሰዋል። ሽግግሩን ብቻ ሳይሆን ከዚያም ባሻገር ስለምንመኘው ሥርዓት የጋራ አማራጭ ቀርቦ እያለ ታዲያ ለምን አማራጭ የለም ይባላል።

ለዚህ ምክንያቱ ግልጽ ይመስለናል። በጋራ ቢነሳ ለኢህአደግና ለባእዳን ደጋፊዎቹ የማይዋጥ የማይተፋ ጥያቄ ይሆን የነበረውን አማራጭ በተግባር ለመተርጎም የጋራ ትግል አይካሄድም ። በትጥቅ ሆነ በሰላማዊ ዘዴ ፤ በህጋዊ ሆነ በህቡእ፤ በፖለቲካም ሆነ በሌሎች ድርጅቶች፤ በግለሰብ ሆነ በስብስቦች አማካኝነት የሚታገሉ ኃይሎች ሁሉ እናምንበታለን የሚሉትን አማራጭ ተግባራዊ ለማድረግ ሰባቱ የፓሪስ ድርጅቶች በትክክል እንዳስቀመጡት ሌሎች አጫፋሪ ጥያቄዎችን ወደ ጎን ትተው በዚህ ወሳኝ ጥያቄ ላይ በጋራ ሲረባረቡ ኖሮ ኢህአደግን የሚይዘው የሚለቀው የሚያሳጣ፤ ጭፍን ባእዳን ደጋፊዎቹን ከሰበብ አስባብ ባሻገር ራሳቸውን መልሰው እንዲጠይቁ የሚገፋፋ ይህ ነው የማይባል ህዝባዊ ማዕበል ይፈጥር ነበር።

ይህንን ካላደርግን ደግሞ ከባሻገሩ ሽግግሩ አስቸግሮንና አቅቶን የኢትዮጵያን ህዝብ የመከራ ቀናት እያራዘምን ፤ የኢህአደግ ሹማምንት እያሾፉብን ፤ ባእዳን ደጋፊዎቻቸው ደግሞ እንደናቁን ቀን ከመግፋት ሌላ አማራጭ አይታየንም።

ቀደም ሲል በቀረቡ ዝግጅቶቻችን ለዚህ የጋራ ትግል መንደርደሪያ ሊሆኑ ይችላሉ በማለት ሰባቱ የፓሪስ ድርጅቶች ያቀረቡትን የጋራ ሰነድና የቀየሱትን የጋራ ትግል አቅጣጫ በተከታታይ አቅርበናል። በዚህም ተመርኩዘን ላደርግነው የጋራ ትግል ጥሪ ከኢትዮጵያም ሆነ ከ አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ የደረሱን ማበረታቻዎች ከጠብቅነው በላይ ሆነው አግኝተናቸዋል። በተደጋጋሚ የሚቀርቡት ጥያቄዎች ታዲያ እንግዲህ ምን ይደረግ ? እኛስ ይህንን ሂደት በምን ዘዴ እናግዝ ? የሚሉ ጥያቄዎች ናቸው። ለዚህም ውይይት እንዲረዳ በሚቀጥሉት ዝግጅቶቻችን አንድ ሌላ ሰነድ ለአድማጮቻችን እናቀርባለን።

ይህ ሰነድ በኢትዮጵያ ደሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት ተረቆና ፀድቆ ለአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት የቀረበውና በምክር ቤቱም ጉባዔ በሙሉ ድምፅ የጸደቀው"ለአዲስ ደሞክራሲያዊ ጅማሮ" የሚለው ታሪካዊ ሰነድ ነው።

ይህ ሰነድ ምን ይዟት አለው? ለደሞክራሲያዊ ኃይሎች በሙሉ የሚያቀርበው የትግል አንድነት ጥሪ ምን ይመስላል ? ስለ ተሰበጣጠሩ የትግል ስልቶች አንድነትና ልዩነትስ ምን ይላል? እነዚህንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ለማጤን እንዲቻል ሰነዱን በተከታታይ ለአድማጮች በቅድሚያ ካቀርብን በኋላ በትግል ላይ ላሉ የፖለቲካና ሌሎች ድርጅቶች እንደዚሁም ለሃገር ተቆርቋሪ ለሆኑ ዜጎች በሙሉ የሰነዱን ተግባራዊነት ለማረጋገጥ መወሰድ ስለሚገባቸው ተጨባጭ እርምጃዎች ሃሳባችንን እንሰነዝራለን ////

ቀስተ ደመና የሰላምና የውንድማማችነት ድምፅ ሬዲዮ
በአጭር ሞገድ (short wave) እንደሚከተለው ይተላለፋል ፤

| ቀን | ሞገድ | ሰዓት | አቅጣጫ |
|---|---|---|---|
| ሐሙስ | 19 ሜትር ባንድ<br>15.365 kHz | በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር<br>ከምሽቱ 1 እስከ 2 ሰዓት | ምስራቅ አፍሪካ<br>ኢትዮጵያ |
| ዓርብ | 19 ሜትር ባንድ<br>5.910 kHz | በአሜሪካን ሰዓት አቆጣጠር<br>ከምሽቱ 9.00 - 10.00 ሰዓት | ሰሜን አሜሪካ<br>ምስራቃዊ ጠረፍ |
| እሁድ | 49 ሜትር ባንድ<br>5.910 kHz | በአውሮፓ ሰዓት አቆጣጠር<br>ከጠዋቱ 9.00-- 10.00(10.00-11.00 ለብሪታንያ) | ምዕራብ አውሮፓ |